# ቅማንትን በተመለከተ ዝርዝር ወቅታዊ ሪፖርታዥ

(ልሣነ ዐማራ- Amhara Press)

ለቅማንት 42 ቀበሌ ተነግሮን ሲደመር 21 ቀበሌ በድብቅ በድምሩ 63 ቀበሌዎችን (12 ቀበሌዎች ለህዝ በዉሳኔ የቀረቡ) ህወሃት/ብአዴን ሸልሟቸዋል። በእነዚህ ቀበሌዎች ላይ የህዝበ ዉሳኔዉ ሳይካሄድ ለምን በተጨማሪ 12ቱ ቀበሌዎች ላይ የህዝበ ዉሳኔዉ እንዲካሄድ ተፈለገ ብሎ አንባቢ መጠየቁ አይቀርም። ለአንባቢ ግልፀ ለማድረግ ከላይ የተጠቀሱት በተለይ በብአዴን የተሰጣቸዉ ቀበሌዎች ላይ አርማጭሆና ጭልጋ ወረዳዎች ላይ የሚገኙና በመልክአ ምድር አቀማመጣቸዉ ተራራማና ለእርሻም ሆነ ለከብት ርባታ የማይመቹ የተሸረሸሩ ቀበሌዎች ናቸዉ። እነዚህን ቀበሌዎች በህወሃት/ብአዴን ከተቸራቸዉ በኃላ ቅማንቶች ያልጠበቁት ነገር ተፈጠረ። እርሱም እጅግ ለም መሬቶቹ የሚገኙት አማራዉ በሚኖርበት መተማ ቋራና ምዕራብ አርማጭሆ ወረዳዎች ነዉ። ከዚህ በፊት ቅማንቶች በእነዚህ ለም መሬቶች ላይ ሰሊጥ ጥጥ የማልማት ከብት የማራባት አማራዊ መብት ነበራቸዉ። ይህንን መብታቸዉን ግን ህወሃት ነጥቆ በተራራ ላይ እንዲወሰኑ አደረገ።

አማራዉም አልተዋለድነም ያሉትን የቅማንት ሰዎች ከሸንፋ ወንዝ በታች እንዳይሻገሩ መተማና ቋራ ምራብ አርማጭሆ ወርደዉ የአማራዉን መሬት መጠቀም እንደማይችሉ በግልጽ አሳወቀ። በአማራዉ ዉሳኔ የበረገገዉ ህወሃት ከትግራይ ክልል በአንቡላንስ እየጫነ ስናይፐርና ክላሽ ለቅማንት ወጣቶች አከፋፈለ። ይህም አልበቃዉም ጉባይ ሌንጫና ጀጀቢት ከሚባሉ ቀበሌዎች የቅማንትን ወጣት ሰብስቦ ወታደራዊ ስልጠና ተሰጣቸዉ የአማራ በሬዎች እየተዘረፉ በቀን 30 በላይ በሬዎች እየታረዱ ስልጠናዉን በትግሬ ጀኔራሎች ወሰዱ። ከዚያም የአማራዉን መሬት በሃይል ለመያዝ ታህሳስ 2008 ዓ.ም በአማራዉ ላይ ጦርነት ታወጀ። ይህ ጦርነት አማራዉን ለማጥፋት የታወጀ ቢሆንም ድል ለአማራዉ ሆነ።

በጦርነት ያልተሳካላቸዉ ህወሃቶች ለቅማንት በማንአለብኝነት አማራዉ ሳይሰማ 21 ቀበሌ ሰጡ። ይህም ህወሃትን አላረካትም 12ለቱን ለምና አምራች የአማራ ቀበሌዎች ለቅማንት ለመስጠት ህወሃት ህዝበ ዉሳኔ ይካሄድ አለች አማራዉም በነቂስ ወጥቶ የምርጫ ካርድ አወጣ። አሁንም ድል ለአማራ ሆነ። በዚህ ተስፋ የቆረጡ ወገኖች የህዝበ ዉሳኔዉን አንፈልግም ማለት ጀመሩ። እኛም አልን ድሮ ነበር እንጅ መጥኖ መደቆስ አሁን ምን ያደርጋል ወጭት ጥዶ ማልቀስ። እናም ከሸንፋ ቀበሌ ዉጭ ህዝበ ዉሳኔዉ ይካሄድባቸዋል በተባሉት ቀበሌዎች የሚኖሩት ቅማንቶች ህዝበ ዉሳኔዉ እንዲካሄድ እንደማይፈልጉ እየተናገሩ ነዉ። ከዚህ ዉሳኔ ላይ የደረሱት አንድም በቅንነት አለዚያም በምርጫ ዉጤቱ ተስፋ በመቁረጥ ሊሆን እንደሚቻል ይገመታል።

ምንም ይሁን ምን ህዝበ ዉሳኔዉ ሊካሄድ የሚቀረዉ አንድ ቀን ብቻ ነዉ። የህዝበ ዉሳኔዉ በሚካሄድባቸዉ 12ቱም ቀበሌዎች የምርጫ ካርድ ያወጣዉ ህዝብ ስብጥር ሲሰላ በሁሉም ጣቢያዎች አማራዉ በከፍተኛ ቁጥር እየመራ ነዉ። አንድ የምርጫ ጣቢያ ላይ 600 አማራ 18 ቅማንት 30 ትግሬ ለወደህከር መግዣ 700 ብር ለእያንዳንዱ ሰዉ የተሰጣቸዉ 170 ጉምዞች (ቅማንት ሲደመር ትግሬ ሲደመር ጉሙዝ 118) እንደሆነ ለማረጋገጥ ችለናል። ይህ የምርጫ ጣቢያ ከሁሉም የምርጫ ጣቢያዎች በጥቃቅንና አነስተኛ የተደራጀ ከፍተኛ የቅማንት መራጭ የተመዘገበበት ጣቢያ እንደሆነ ከመዝጋቢዎች ለማረጋገጥ ችለናል። ይህ በእንዲህ እያለ በጭልጋ 4 ቀበሌዎች ምርጫዉን እንደማይሳተፉና ራሳቸዉን እንዳገለሉ ታዉቋል።

መልክት ለጎንደር አማራ
======
አንዳች ታምር ካልተፈጠረ በቀር ለምርጫ በተመዘገበዉ ህዝብ ስብጥር ሲሰላ በ12ቱም ቀበሌዎች ምርጫዉ በአማራዉ አሸናፊነት እንደሚደመደም ተረጋግጧል። ስለሆነም አማራዉ ከምርጫ በኃላ ምን ማድረግ አለበት ከተባለ ያለ ህዝበ ዉሳኔ ወደ ቅማንት የተካለሉትን 21 ቀበሌዎች ሲደመር 42 ቀበሌ በጥቅሉ 63 ቀበሌዎች በህወሃትና ብአዴን ቀጥተኛ ትዛዝ ወደ ቅማንት ልዩ ወረዳ ተከልለዋል። ከላይ በጠቀስኳቸዉ ለቅማንት የተሰጡት 63 ቀበሌዎች ዉስጥ አማራዉ በብዛት ተሰባጥሮ ይኖራል። ስለሆነም አማራዉ የራሱን ኮሚቴ በመምረጥ በ63ቱም ቀበሌዎች የህዝበ ዉሳኔ እንዲካሄድ መንግስት በነካ አፉ እንዲፈጽመዉ የማስገደድ ስራ መስራት አለበት።አማራዉ አሁንም ከትናንቱ ይሉኝታዉ ተላቆ ትምህርት መዉሰድ እጅግ አማራዉ ባይጠላቸዉም የተወሰኑ ለአማራዉ ቀና አመለካከት ያላቸዉ እንዳሉ እንደተጠበቀ ሆኖ በአማራ ጥላቻ እጅግ የሰከሩ አማራዉን ለማጥፋት የማይተኙ አንዳንድ ቅማንቶችና ትግሬዎች እንዳሉ መረዳት አለበት። በእርግጥ አማራዉ ከትናንቱ ዛሬ እየተማረ የሚፈጸምበት ግፋ በራሱ እያስተማረዉ መሆኑ ግልጽ ቢሆንም ማስታወሱ ግን የአማራነት ግዴታችን ነዉ።
መልክት ለላኮመልዛ አማራዎች
==============
ወያኔ በሙብቱ ያለህዝበ ዉሳኔ ወደ ትግራይ ክልል የተካለለዉና አማራዉ ሳይፈልግ የትግሬ ማንነት እንዲጫንበትና ትግርኛ እንዲናገር በትግርኛ እንዲማርና እንዲዳኝ መደረጉ ኢሰባዊና ህገ ወጥነት ስለሆነ አማራዉ የራሱን ኮሚቴ በመምረጥ በአስቸኳይ መንግስት ለቅማንት የፈቀደዉን ህዝበ ዉሳኔ ራያ አዘቦ፣ አፍላ፣መሆኒና አላማጣ ላይ ተግባራዊ እንዲያደርግ ማስገደድ አማራዊ ግዴታችን ነዉ።
አዲሱ የአማራ ትዉልድ የአባቶቹን ታሪክ ያደሳል!!